# በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማርያም በመባል የሚታወቁ ስሞችና ጥቅሶቻቸው የሚገኙበት ቦታ፦

የዚህ ትምህርት አስፈላጊነት ስምንቱም ማርያሞች የራሳቸው የሆነ ሥራ እና ታሪክ ያላቸው በመሆናቸው የአንዱን ታሪክ እና ሥራ ከሌላው ሥራ እና ታሪክ ጋር በማደባለቅ ለአምላክ እናት የተሰጠውን የሥራ ድርሻ እና ታሪክ ለማርቆስ እናት ፤ እንዲሁም ለሌሎቹ ማርያሞች የተሰጠውን የሥራ ድርሻ እና ታሪክ ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም በመስጠት የመጽሐፍ ቅዱሱን ትክክለኛ ይዘት ካለማገናዘብ ለምንጠቀም ሰዎች ማረሚያና ማስተካከያ ለመስጠት ነው። በሌላ መልኩም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ዓይነት ስሞች ያላቸው ብዙ ሐዋርያት እና ቅዱሳን ሰዎች ወይም ባለ ታሪኮች ስላሉ ከወዲሁ ግንዛቤ በመውሰድ ማን ምን እንደሆነና ያለውም የሥራ ድርሻና ታሪክ የትኛው እንደሆነ ጠንቅቆ ለማወቅ አንባብያን ትኩረት እንዲሰጡበት ለማሳሰብ ጭምር ነው።

## ፩- ማርያም የጌታችን የአምላካችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት፦

### ☞ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ስለመገኘትዋ ለዮሴፍም የጌታ መልአክ በሕልም እንደታየው፦

የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች። እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ስላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ። እርሱ ግን ይህን ሲያስብ ፣ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው ፣ እንዲህም አለ። የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ፣ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። በነቢይ ከጌታ ዘንድ። እነሆ ፣ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ፣ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል ፣ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው። ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ ፤ እጮኛውንም ወሰደ ፤ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው። ማቴ. ፩ ፣ ፲፰-፳፭

### ☞ መልአኩ ገብርኤል እንዳበሠራት ወደ ኤልሳቤጥም ዘንድ እንደሄደች ኤልሳቤጥም እንደ ተሳለመቻት፦

በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ፣ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ ፣ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ። መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ ፣ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ፣ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው ፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና ፤ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም ፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል ፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል ፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፣ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። ማርያምም መልአኩን። ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ ፣ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች ፣ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው ፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ። ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች ፣ ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት። ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ፣ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ

አለች። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ ፣ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው። የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ ፣ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና። ከጌታ ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት። ማርያምም እንዲህ አለች። ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች ፣ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች ፤ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም ፣ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ፤ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጎአልና ፤ ስሙም ቅዱስ ነው። ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል። በክንዱ ኃይል አድርጎአል ፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል ፤ ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል ፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል ፤ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል ፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል። ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ ፣ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘላለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቶአል። ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርስዋ ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤትዋም ተመለሰች። ሉቃ. ፩ ፥ ፵፮-፶፮

### ☞ በቃና ዘገሊላ ስለነበረው ድንቅ ተዓምራት፦

በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ ፣ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች ፤ ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ። የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት። የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው። ኢየሱስም አንቺ ሴት ፣ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት። እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው። አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ስድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር ፣ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንስራ ይይዙ ነበር። ኢየሱስም። ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው። አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ስጡት አላቸው ፤ ሰጡትም። አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም ፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር ፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ። ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል ፣ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን ፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው። ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ ፤ ክብሩንም ገለጠ ፣ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ። ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ ፣ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ። ዮሐ. ፪ ፥፩-፲፪

### ☞ እናትህና ወንድሞችህ በውጭ ቆመዋል ብለው የተናገሩትና የመለሰላቸው መልስ፦

እናቱና ወንድሞቹም መጡ በውጭም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት። ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበሩና። እነሆ ፣ እናትህ ወንድሞችህም በውጭ ቆመው ይፈልጉሃል አሉት። መልሶም። እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? አላቸው። በዙሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩትም ተመለከተና። እነሆ እናቴ ወንድሞቼም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ ፣ እርሱ ወንድሜ ነው እኅቴም እናቴም አለ። ማር. ፫ ፥፴፩-፴፭

### ☞ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው እንዳለችው፦

ይህንም ሲናገር ፣ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ። የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው። እርሱ ግን። አዎን ፣ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው አለ። ሉቃ. ፲፩ ፥፳፯-፳፰

### ☞ በመስቀሉ አጠገብ ቆማ እንደነበር፦

ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ ፣ የእናቱም እኅት ፣ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም ፣ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን። አንቺ ሴት ፣ እነሆ ልጅሽ አላት። ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን። እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት። ዮሐ. ፲፱ ፥ ፳፭-፳፯

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

☞ **ከሐዋርያት ጋር አብራ በጸሎት ትተጋ እንደነበር፡-**

እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር። ሐዋ. ፩ ፥ ፲፬

## ፪- መግደላዊት ማርያም፡-

☞ **ከሌሎች ሴቶች ጋር ጌታን ታገለግል እንደነበር፡-**

፲፪ ሐዋርያት ከእርሱ ጋር ነበሩ ፥ ከክፉዎች መናፍስትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች ፤ እነርሱም ፯ አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም ፥ ሉቃ. ፰ ፥፪

☞ **በስቅለቱ ጊዜ፡-**

ሴቶችም ደግሞ በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር ፤ ከእነርሱም በገሊላ ሳለ ይከተሉትና ያገለግሉት የነበሩ መግደላዊት ማርያም የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት ማርያም ሰሎሜም ነበሩ ፥ ከእርሱም ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የወጡ ሌሎች ብዙዎች ሴቶች ነበሩ። ማር. ፲፭ ፥፵

ከእነርሱም መግደላዊት ማርያምና የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ። ማቴ. ፳፯ ፥፶፮

ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ ፥ የእናቱም እኅት ፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም ፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር። ዮሐ. ፲፱ ፥፳፭

☞ **በቀብሩ ጊዜ፡-**

መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር።
ማር. ፲፭ ፥፵፯
መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛይቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ።
ማቴ. ፳፯ ፥፷፩

☞ **በባዶው መቃብር፡-**

- ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብር መጡ። እርስ በርሳቸውም። ድንጋዩን ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይባባሉ ነበር ፤ ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና ፤ አሻቅበውም አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ። ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ። እርሱ ግን። አትደንግጡ ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ ፤ ተነሥቶአል ፥ በዚህ የለም ፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ። ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም። ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል ፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው። መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልነገሩም። እነርሱም ያዘዛቸውን ሁሉ ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ላሉት በአጭሩ ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው። ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ ፥ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ። እርስዋ ሄዳ ከእርሱ ጋር ሆነው ለነበሩት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ ሳሉ አወራችላቸው ፤ እነርሱም ሕያው እንደ ሆነ ለእርስዋም እንደ ታያት ሲሰሙ አላመኑም። ማር. ፲፮ ፥፩-፲፩

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

- በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። እነሆም ፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በለዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም ፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ ፥ እነሆም ፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። እነሆም ፥ ነገርኋችሁ። በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ። እነሆም ፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ። አትፍሩ ፤ ሄዳችሁ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ ፥ በዚያም ያዩኛል አላቸው። ማቴ.፳፰ ፥፩-፲

- ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ሉቃ. ፳፬ ፥፲

☞ **በትንሣኤው ጊዜ፦**

- ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ ፥ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ። ማር. ፲፮ ፥፱

- ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች። እየሮጠችም ወደ ስምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር መጥታ። ጌታን ከመቃብር ወስደውታል ወዴትም እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው። ስለዚህ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ። ሁለቱም አብረው ሮጡ ፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደ ፊት ሮጠና አስቀድሞ ከመቃብሩ ደረሰ ፤ ዝቅም ብሎ ቢመለከት የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ ፥ ነገር ግን አልገባም። ስምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ ወደ መቃብሩም ገባ ፤ የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ ፥ ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው በአንድ ስፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ። በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ ፥ አየም ፥ አመነም ፤ ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁም ነበርና። ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው ደግሞ ሄዱ። ዮሐ. ፳ ፥፩-፲

## ፫- ማርያም (የቢታንያዋ) የማርታና የአልዓዛር እኅት፦

☞ **አልዓዛርን ከሞት እንዳስነሣውና ማርታና ማርያም እንዳነጋገሩት፦**

- ከማርያምና ከእኅትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ታሞ ነበር። ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጕርዋ ያበሰችው ነበረች ፤ ወንድምዋም አልዓዛር ታሞ ነበር። ስለዚህ እኅቶቹ ጌታ ሆይ ፥ እነሆ የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ እርሱ ላኩ። ኢየሱስም ሰምቶ። ይህ ህመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ። ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር። እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ዋለ ፤ ከዚህም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ። ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው። ደቀ መዛሙርቱ። መምህር ሆይ ፥ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር ፥ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን? አሉት። ኢየሱስም መለሰ። ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን? በቀን የሚመላለስ ቢኖር

የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም ፤ በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለ ሌለ ይሰናከላል አላቸው። ይህን ተናገረ ፤ ከዚህም በኋላ። ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል ፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላስነሣው እሄዳለሁ አላቸው። እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ። ጌታ ሆይ ፥ ተኝቶስ እንደ ሆነ ይድናል አሉት። ኢየሱስስ ስለ ሞቱ ተናግሮ ነበር ፤ እነርሱ ግን ስለ እንቅልፍ መተኛት እንደ ተናገረ መሰላቸው። እንግዲህ ያን ጊዜ ኢየሱስ በግልጥ። አልዓዛር ሞተ ፤ እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል ፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ አላቸው። ስለዚህ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ለባልንጀሮቹ ለደቀ መዛሙርት ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ አለ።

ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እስከ አሁን አራት ቀን ሆኖት አገኘው። ቢታንያም አሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ለኢየሩሳሌም ቅርብ ነበረች። ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር። ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች ፤ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር።

ማርታም ኢየሱስን ጌታ ሆይ ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር ፤ አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው። ኢየሱስም ወንድምሽ ይነሣል አላት። ማርታም በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።

ኢየሱስም ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ፤ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት። እርስዋም። አዎን ጌታ ሆይ ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው። ይህንም ብላ ሄደች እኅትዋንም ማርያምን በስውር ጠርታ። መምህሩ መጥቶአል ይጠራሽማል አለቻት። እርስዋም በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሣች ወደ እርሱም መጣች ፤

ኢየሱስም ማርታ በተቀበለችበት ስፍራ ነበረ እንጂ ገና ወደ መንደሩ አልገባም ነበር። ሲያጽናኑአት ከእርስዋ ጋር በቤት የነበሩ አይሁድም ማርያም ፈጥና እንደ ተነሣችና እንደ ወጣች ባዩ ጊዜ ፥ ወደ መቃብር ሄዳ በዚያ ልታለቅስ መስሎአቸው ተከተሉአት። ማርያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ። ጌታ ሆይ ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው። ኢየሱስም እርስዋ ስታለቅስ ከእርስዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ ፤ ወዴት አኖራችሁት? አለም። እነርሱም። ጌታ ሆይ ፥ መጥተህ እይ አሉት።

ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ። ስለዚህ አይሁድ። እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ አሉ። ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ። ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን ደግሞ እንዳይሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን? አሉ።

ኢየሱስም በራሱ አዝኖ ወደ መቃብሩ መጣ ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ ፤ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር። ኢየሱስ ድንጋዩን አንሡ አለ። የሞተውም እኅት ማርታ። ጌታ ሆይ ፥ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው። ኢየሱስ ብታምኚስ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዩ አልነገርሁሽምን? አላት። ድንጋዩንም አነሡት። ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ አባት ሆይ ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ። ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ።

ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ አልዓዛር ሆይ ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ። የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር። ኢየሱስም ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው። ዮሐ. ፲፩ ፥ ፩-፵፬

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A) 

☞ **በከበረ የናርዶስ ሽቱ የኢየሱስን እግር እንደቀባች፡-**

➢ ከፋሲካም በፊት በስድስተኛው ቀን ኢየሱስ ከሙታን ያስነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ። በዚያም እራት አደረጉለት ፤ ማርታም ታገለግል ነበር ፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ። ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወስዳ የኢየሱስን እግር ቀባች ፤ በጠጉርዋም እግሩን አበሰች ፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ። ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የስምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ። ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሽጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለ ምን ነው? አለ። ይህንም የተናገረ ሌባ ስለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም ፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለ ነበረ ነው። ኢየሱስም ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት ፤ ድሆችስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና ፣ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ። ዮሐ.፲፪ ፥ ፩-፰

## <u>፬- ማርያም የያዕቆብና የዩሳ እናት፡-</u>

☞ **በገሊላ ሳለ ያገለግሉትና ይከተሉት ከነበሩት አንዷ፡-**

➢ ሴቶችም ደግሞ በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር ፤ ከእነርሱም በገሊላ ሳለ ይከተሉትና ያገለግሉት የነበሩ መግደላዊት ማርያም የታናሹ ያዕቆብና የዮሳም እናት ማርያም ሰሎሜም ነበሩ ፣ ከእርሱም ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የወጡ ሌሎች ብዙዎች ሴቶች ነበሩ። ማር. ፲፭ ፥፵-፵፩

☞ **በስቅለቱ በቀብሩና በባዶው መቃብር ጊዜ፡-**

➢ መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር። ማር. ፲፭ ፥፵፯

➢ ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ። ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብር መጡ። እርስ በርሳቸውም። ድንጋዩን ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይባባሉ ነበር ፤ ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና ፤ አሻቅበውም አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ። ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ። እርሱ ግን። አትደንግጡ ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ ፤ ተነሥቶአል ፣ በዚህ የለም ፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ስፍራ። ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም። ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል ፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው። መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልነገሩም። እነርሱም ያዘዛቸውን ሁሉ ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ላሉት በአጭሩ ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጃቸው ላከው። ማር. ፲፮ ፥፩-፰

➢ ከእነርሱም መግደላዊት ማርያምና የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ። ማቴ. ፳፯ ፥፶፮

➢ በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ። እነሆም ፣ የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ። ጠባቂቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና ፤ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም ፤ የተኛበትን ስፍራ ኑና እዩ። ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ ፥ እነሆም ፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው። እነሆም ፥ ነገርኋችሁ። በፍርሃትና በታላቅ ደስታም ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ ፥ ለደቀ መዛሙርቱም ሊያወሩ ሮጡ። ማቴ. ፳፰ ፥፭-፰

- ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ። ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት ፥ ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ ፥ እነሆ ፥ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ ፥ እንዲህ አሉአቸው። ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ። ቃሎቹንም አሰቡ ፥ ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው። ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ሉቃ. ፳፬ ፥፩-፲

## ፫- ማርያም የማርቆስ እናት፦

☞ **ጴጥሮስ በንጉሥ ሄሮድስ ዘመን በወኅኒ ሳለ በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ብዙዎች ጸሎት ያደርጉ እንደነበርና ጴጥሮስም በእግዚአብሔር መልዓክ አማካኝነት ከወኅኒ እንደወጣ የሚገልጽ፦**

- በዚያም ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ጫነባቸው። የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው። አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጨምሮ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው። የቂጣ በዓልም ወራት ነበረ። በያዘውም ጊዜ ወደ ወኅኒ አገባው ከፋሲካም በኋላ ወደ ሕዝብ ያወጣው ዘንድ አስቦ እያንዳንዱ አራት ወታደሮች ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት ጭፍራ ክፍል አሳልፎ ሰጠው።

  ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር ፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር ፤ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር። እነሆም ፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና። ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ። መልአኩም። ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው ፥ እንዲሁም አደረገ። ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው ፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም።

  የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ ፤ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው ፤ ወጥተውም አንዲት ስላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ። ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ። ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ። ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ። ጴጥሮስም የደጁን መዝጊያ ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የሚሉአት አንዲት ገረድ ትሰማ ዘንድ ቀረበች ፤ ሐዋ. ፲፪ ፥፮-፲፫

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A)

- ባስተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ። ሐዋ. ፲፪ ፥፲፪ (የማርቆስ እናት ማርያም)

## ፭- ማርያም የቀልዮጳ ሚስት፦

☞ **በጌታ መስቀል ሥር እንደነበረች፦**

- ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ ፥ የእናቱም እኅት ፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም ፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር።
  ዮሐ. ፲፱ ፥ ፳፭

## ፮- ማርያም የሙሴና የአሮን እኅት፦

☞ **ሕፃን ሙሴን በባሕር ተጥሎ ሳለ ትከታተለችው እንደነበር፦**

- እኅቱም የሚደረግበትን ታውቅ ዘንድ በሩቅ ቆማ ትጎበኘው ነበር። የፈርዖንም ልጅ ልትታጠብ ወደ ወንዝ ወረደች ፤ ደንገጥሮችዋም በወንዝ ዳር ይሄዱ ነበር ፤ ሣጥኑንም በቄጠማ ውስጥ አየች ፥ ደንገጥርዋንም ልካ አስመጣችው። በከፈተችውም ጊዜ ሕፃኑን አየች ፥ እነሆም ሕፃኑ ያለቅስ ነበር ፤ አዘነችለትም። ይህ ከዕብራውያን ልጆች አንድ ነው አለች። እኅቱም ለፈርዖን ልጅ። ሕፃኑን ታጠባልሽ ዘንድ ሄጄ የምታጠባ ሴት ከዕብራውያን ሴቶች ልጥራልሽን? አለቻት። የፈርዖንም ልጅ። ሂጂ አለቻት ፤ ብላቴናይቱም ሄዳ የሕፃኑን እናት ጠራች።
  ዘጸ. ፪ ፥ ፬-፰

☞ **ቀይ ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ ስለመዘመርዋ፦**

- የአሮን እኅት ነቢይቱ ማሪያምም ከበሮ በእጅዋ ወሰደች ፤ ሴቶችም ሁሉ በከበሮና በዘፈን በኋላዋ ወጡ። ማርያምም እየዘመረች መለሰችላቸው። በክብር ከፍ ከፍ ብሎአልና ለእግዚአብሔር ዘምሩ ፤ ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ጣለ።
  ዘጸ.፲፭ ፥፳-፳፩

- ከግብጽ ምድር አውጥቼሃለሁ ፥ ከባርነት ቤትም ተቤዥቼሃለሁ ፤ በፊትህም ሙሴንና አሮንን ማርያምንም ልኬልህ ነበር።
  ሚክ. ፮ ፥፬

☞ **ሙሴ ኢትዮጵያዊቷን ስላገባ እንዳጉረመረመችና በለምፅ እንደተመታች፦**

- ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማርያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ። እነርሱም። በውኑ እግዚአብሔር በሙሴ ብቻ ተናግሮአልን? በእኛስ ደግሞ የተናገረ አይደለምን? አሉ ፤ እግዚአብሔርም ሰማ። ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ። እግዚአብሔርም ወዲያው ሙሴንና አሮንን ማርያምንም። ሦስታችሁ ወደ መገናኛው ድንኳን ውጡ ብሎ ተናገረ ፤ ሦስቱም ወጡ። እግዚአብሔርም በደመና ዓምድ ወረደ ፥ በድንኳኑም ደጃፍ ቆመ ፤ አሮንንና ማርያምን ጠራ ፥ ሁለቱም ወጡ። እርሱም። ቃሌን ስሙ ፤ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር ፥ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ። ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም ፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ ፥ በምሳሌ አይደለም ፤ የእግዚአብሔርንም መልክ

ያያል ፤ በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለ ምን አልፈራችሁም? አለ። እግዚአብሔርም ተቈጥቶባቸው ሄደ።

- ደመናውም ከድንኳኑ ተነሣ ፤ እነሆም ፥ ማርያም ለምጻም ሆነች ፥ እንደ አመዳይም ነጭ ሆነች ፤ አሮንም ማርያምን ተመለከተ ፥ እነሆም ፥ ለምጻም ሆና ነበር። አሮንም ሙሴን። ጌታዬ ሆይ ፥ ስንፍና አድርገናልና ፥ በድለንማልና እባክህ ፥ ኃጢአት አታድርግብን። ከእናቱ ሆድ በወጣ ጊዜ ግማሽ ሥጋው ተበልቶ እንደ ሞተ እርስዋ አትሁን። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር እየጮኸ። አቤቱ ፥ እባክህ ፥ አድናት አለው።

  እግዚአብሔርም ሙሴን። አባትዋ ምራቁን በፊትዋ ቢተፋባት ስንኳ ሰባት ቀን ታፍር ዘንድ ይገባት ነበር ፤ ሰባት ቀን ከሰፈር ውጭ ተዘግታ ትቀመጥ ፥ ከዚያም በኋላ ትመለስ አለው። ማርያምም ከሰፈር ውጭ ሰባት ቀን ተዘግታ ተቀመጠች ፤ ማርያምም እስክትመለስ ድረስ ሕዝቡ አልተጓዙም። ዘኍ. ፲፪ ፥ ፩-፲፭

- አምላክህ እግዚአብሔር ከግብፅ በወጣችሁ ጊዜ በመንገድ ሳላችሁ በማርያም ላይ ያደረገውን አስብ።
  ዘዳ. ፳፬ ፥ ፱

☞ ማርያም በቃዴስ ምድረ በዳ እንደሞተች፡-

የእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ በመጀመሪያው ወር ወደ ጺን ምድረ በዳ መጡ ፤ ሕዝቡም በቃዴስ ተቀመጡ ፤ ማርያምም በዚያ ሞተች ፥ በዚያም ተቀበረች። ዘኍ. ፳ ፥ ፩

## ፰- ማርያም ከካሌብ ጎሳ የነበረችው፡-

☞ የሁር ማርያምን ስለ መውለዱ፡-

የዕዝራም ልጆች ዬቴር ፥ ሜሬድ ፥ ዔፌር ፥ ያሎን ነበሩ ፤ ዬቴርም ማርያምን ፥ ሸማይን ፥ የኤሽትምዓን አባት ይሽባን ወለደ። መጽ. ዜና ቀዳማዊ. ፬ ፥፲፯

Copyright © 2009 Debre Selam Medhanealem Ethiopian Orthodox Tewahedo Church 4401 Minnehaha Avenue South Minneapolis, Minnesota 55406 Tel. (612) 721-1222 (U.S.A) www.debreselam.net 